የምፅዐቱ የምሥራች

ቅጽ 65 ቁጥር 3(771) «በቅዱስ ስሙም ታምነናልና አቤቱ ምህረትህ በላያችን ትሁን» (መዝሙር 32፡-22)

መንፈሳዊ ተሀድሶ ሀገርን ያድናል

ይህንን ርዕስ ከማንበባችሁ በፊት እግዚአብሔር ስለሀገር የሰጣቸውን የተስፋ ቃሎች ከመፅሐፍ ቅዱስ ተመልከቱ:: «እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ ምስጉን ነው» (መዝሙር 32:12)

«ፅድቅ ሕዝብን ከፍ ከፍ ታደርጋለች፣ ኃጢአት ግን ሕዝብን ታስነውራለች» (ምሳሌ 14፡-34)::

«ትዕዛዙንና ፍርዱን ሥርዓቱንም ባለመጠበቅ አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሣ ተጠንቀቅ» (ዘዳግም 8÷11)

«ኃጢአተኞች ወደሲኦል ይመለሳሉ እግዚአብሔርንም የሚረሱ አሕዛብም ሁሉ» (መዝሙር 9÷17) «እግዚአብሔርን የምትረሱ እናንተ ይህን አስተውሉ አለዚያ ይነጥቃል የሚያድንም የለም» (መዝሙር 50÷22)

በታሪክ ተመራማሪዎች ግኝት እንደተረጋገጠው ታላላቅ መንግሥታትና ሥልጣኔዎች ለወድቀት የሚበቁት በደልና ግፉ ተስፋፍቶባቸው ከእግዚአብሔር በጐ ዓላማና መንገድ በወጡ ጊዜ ለመሆኑ የሮማ ሥልጣኔ አወዳደቅ ትልቅ ምስክር ነው::

በመፅሐፍ ቅዱስ በዝርዝር እንደተፃፈው አንድ ሀገር ከመውደቁ በፊት ጐልተው የሚታዩ ምልክቶች የማህበራዊ ቀውስ፣ የኢኮኖሚ ቀውስና የሥነ-ልቡና ቀውስ ናቸው::

በአንድ ሀገር ላይ ሕግና ሥርዓት ጠፍቶ ክፍ ሰዎች ስልጣን በሚጨብጡበት ጊዜ የኢኮኖሚና የፓለቲካ ቀውስ እንደሚከተሉ የሞራልና የሥነ-ልቡና ውድቀትም እንደሚሰፍን በተደጋጋሚ በዓለም ታሪክ ታይቷል::

ፍትህና በጐነት ከመንግስታት ሲርቅ ሕዝብ መረን እየሆነ፣ እራስ ወዳድነት ይነግስና አንዱ ሌላወን በጥላቻና በክፋት እየተመለከተ ለመሰፋፋት ተፈላላጊ ይሆናሉ::

አንድ ትውልድና ሀገር ያለፈውን ታሪካቸውን በመመርመር ለሚቀጥለው ዘመን መልካምና በጐ ራዕይ ሊኖረው እንደሚችል የጥበብ ሁሉ ምንጭ የሆነው መፅሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፤ «ዘመናችን በምድር ላይ እንደጥላ ነውና እኛ የትናንት ብቻ ነን፣ ምንም አናውቅም፣ ስለዚህ የቀደመውን ትውልድ ጠይቅ፣ አባቶቻቸውም ለመረመሩት ነገር ትጋ» (እዮብ 8÷9)

አርስቶትል የተባለው የጥንት ግሪክ ፈላስፋ ስላለፉ ጊዜያት አስተማሪነት ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማረው ሰው ይህንን ብሏል «ታሪክን የሚያውቁ ስህተትን ይደግማሉ»::

በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን ኢትዮጵያና መላው ዓለም ከላይ በተዘረዘሩትና በመሳሰሉት ችግሮችና አስከፊ ውጤቶች የተነሳ በጭንቅ ላይ እንደሚገኙ ከሁላችንም የተሰወረ አይደለም::

ስለዚህ በኃጢአት ምክንያት ሕግን ተላልፎ የሰው ዘር ከእግዚአብሔር በመለየቱ ለሞት ፍርድ መዳረጉ ያላዘነውና ማንም እንዳይጠፋ

የሚፈልገው እግዚአብሔር ለዚህ መውጫ መንገድ አለው። እርሱም መንፈሳዊ ተሀድሶ ነው። «አቤቱ በዓመታት መካከል ትታወቅ በመዓት ጊዜ ምሕረትህን አስብ» (መዝሙር 9÷1-8)

«የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ» ስለሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ ስለአህጉራችን አፍሪካ (ኩሽ) እጅግ የበዙ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች የተሰጡና በታሪክም ከመጀመሪያዎቹ የሥልጣኔ ጀማሪዎች የምንቆጠር ነን።

ነገር ግን አሁን ያለንበት ሁኔታ በጣም አሳዛኝ እጅግ አሰቃቂ በነፍስም በስጋም የተጐሣቆልን ለመሆናችን የምእራቡ ዓለም የመገናኛ ብዙሃን አደንቋሪ መልእክት ብቻ ሳይሆን እራሳችንን በእራሣችን በማየት የምናረጋግጠው ሀቅ ነው። ግን ለምን?

ኢትዮጵያም ሆነች አፍሪካ በመንፈሳዊና በስጋዊ ጉዳዮች ተሀድሶን አልተለማመዱም። የአውሮፓና ስሜን አሜሪካ ታላቅ ሥልጣኔና ብልፅግና የተከተለው ግን በታላላቆቹ የመንፈሳዊና የኪነጥበብ ተሀድሶዎች (ሪፎርማሽንና ሬይኔሰንስ) ለመሆኑ የዓለም ታሪክ ያረጋግጥልናል። እኛ ግን ተሀድሶ የሚያራምዱ ሊቃውንቶቻችንና መሪዎቻችንን ሲመቸን እያነቅንና ስንገድል፣ ሣይመቸን ደግሞ ለወጭ ጠላት መንገድና መረጃ እያቀረብን አስፈጅተናል።

በምቀኝነትና በቅናት የተሞላው ወገናችን ከእግዚአብሔር ቤት ጀምሮ ተፎካካሪውንና በችሎታ የሚበልጠወን በሚርት፣ በጥላ ወጊ፣ በንደርቢ ሲያሣድድ፣ ሲገድል ከዚህ ደርሰናል። ይህንንም የመገዳደልና የመጠፋፋት ተንኮላችንን እንደመልካም ጀብዱ እንመካበታለን።

አሁን ግን ከትውልድ ወደትውልድ በሚተላለፉ መርገም ተይዘን የዓለም መሣለቂያ በመሆናችን ፊታችንን ወደጌታ በመመለስ በእውነተኛ ንስኃ ከመታደስ የተሻለ አንዳች አማራጭ የለንምና በእውነት ወደጌታ እንመለስ! እንታደስ! «ፊታቸውንም ሣይሆን ጀርባቸውን ሰጡኝ፣ በመከራቸው ጊዜ ግን ተነስተህ አድነን ይላሉ» (ኤርምያስ 2÷27)።

ለወንጌልና ለእግዚአብሔር ቃለ-ምህላ አደባባዩን የከለከለ ሕዝብ ጭንቅና መከራ ሲበዛበት ግፍና እርዛት ሲያይልበት «ኢትዮጵያ ታበፅህ ወደ እግዚአብሄር» «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች» (መዝሙር 67÷31) ይላል።

እንደምሳሌያችን «ቀድሞ ነበር እንጅ አልሞ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ» እንዳይሆንብን መከራና ጉስቁልናው በእርማችን በመተላለፋችን የተነሳ ሲደርስብን «ፈጣሪ ድረስ» እያልን ከንቱ ፀሎትና ሰብዓ ከማድረግ ይልቅ እግዚአብሔርን በሁሉም ሰዓትና ጊዜ መልዕክተኞቹን በላከልን ወቅት ሰምተነው እንስተካከል እንታደስ!

«የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፣ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም (ትንቢተ ኢሳይያስ 59÷1)

መልዕክት ከአሣታሚው
(ሪክ ካርማይክል)

«በእየሩሳሌም አደባባይ የሐሤት ድምፅና የደስታ ድምፅ የወንድ ሙሽራ ድምፅና የሴት ሙሽራ ድምፅ ይሰማል» እግዚአብሔር ቸር ነውና፣ ምህረቱም ለዘለዓለም ነውና (ኤርሚያስ 33፡11)።

በትንቢተ ኤርሚያስ መፅሐፍ ላይ ታሪክ የተገለፀው የእስራኤል ሕዝብ ለሰባ ዓመታት በባቢሎን ምርኮ የማቀቀ ሲሆን ነብዩ ለዚህ ተስፋ ለቆረጠ ሕዝብ የእግዚአብሔርን የማዕናኛ ቃል በማምጣት አበረታቷቸዋል። በትክክል በገለአድ ከእግዚአብሄር የሆነ ፈዋሽ መልዕክተኛ ለእግዚአብሄር ሕዝብ መኖሩን አመልካች የአፅንኦት ጥያቄ ነው። ዛሬም ለኢትዮጵያ ነገሮች ተወሳስበው፣ ክፋት ነግሶ ጥላቻና መገዳደል በሰፈነበት ሰዓት በኢትዮጵያ ሐኪም የለምን? ለሚለው ጥያቄ መልሳችን ታላቁ ሐኪም ፈዋሹ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንላለን። በኤርምያስ ጊዜ የነበረው መከራ በዛሬዋ ኢትዮጵያም አለ። በኤርሚያስ ጊዜ እስራኤልን ከምርኮ የታደገ እግዚአብሔር ዛሬም ኢትዮጵያን ሊታደጋት፣ ፍቅርን ሰላምን በረከትንና አንድነትን ሊቀዳጃት የሚሳነው አንዳች የለም «ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም» (ሉቃስ 1÷37)

በዚያን ጊዜ የእስራኤል መሪዎች ስለነበሩበት ከተማ የተነገረው የትንቢት ቃል ዛሬም ለሀገራችን ሊነገር የሚችል ሕያው ቃል ነው።

«ይህች ከተማ የምትቀሠፍ ናት መካከልዋ ሁሉ ግፍ ብቻ ነው። በጉድጓድ ውኃ እንደሚፈልቅ እንዲሁ ክፋትዋ ከእርስዋ ዘንድ ይፈልቃል» (ኤርሚያስ 6÷6)

እግዚአብሔር በየዘመናቱ ለሚወደው ሕዝቡ መልዕክቱንና ተግሣፁን የሚልከው ሕዝቡ ከገባበት የክፋትና የኃጢአት መንገድ ተመልሶ እርሱ ወደአዘጋጀለት መንገድ እንዲመለስ ባለው እቅድ መሠረት ነው።

የእግዚአብሔር በረከትና ተግሣፅ ዛሬም አልተቀየረም። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በመረጣቸው አገልጋዩቹ እርምትን ምክርን ሲልክ ከቆየ በኋላ በኃለኛው ዘመን ግን በአንድ ልጁ በጌታችንና በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕያው ቃሉ በሚገባ ተነግሮናል። (ዕብራውያን 1 ÷2)

በዚህ በአዲስ ኪዳን የመጨረሻው ዘመን ጌታ እግዚአብሔር የሚነግረን አሁንም መንገዳችንን እንድናቀና ከጥፋት እንድንመለስ ነው።

ቤተሰብ ሲቃናና ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ማህበረሰቡም ይመለሳል፤ ማህበረሰቡ ወደ እግዚአብሔር ከተመለሰ ደግሞ ሀገርም ትቀናለች፤ ሀገሮችም ወደ ጌታ ከተመለሱ ምድራችን በአጠቃላይ እግዚአብሔርን በማወቅና በመፍራት ተሞልታ፣ ሰላም፣ ፍትህ በረከትና አንድነት ይሰፋንልናልና።«እኔ የሥጋ ለባሽ ሁሉ አምላክ ነኝ፤ በውኑ እኔን የሚያቅተኝ ነገር አለን» (ኤርምያስ 32÷26)

ዘመኑን ስለመዋጀት

«ደመና ከምእራብ ሲወጣ ባያችሁ ጊዜ ወዲያው ዝናብ ይመጣል ትላላችሁ፤ እንዲሁም ይሆናል፤ በአዜብም ነፋስ ሲነፍስ ትኩሳት ይሆናል ትላላችሁ ይሆንማል። እናንተ ግብዞች የምድሩና የሰማዩን ፊት ልትመረምሩ ታውቃላችሁ። ነገር ግን ይህን ያለንበት ዘመን የምንመረምረው እንዴት ነው? (ሉቃ 12፣54)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘመኑን ምልክት የሚያውቁትን የዚያን ዘመን ሰዎች እንደዚህ የገሰፃቸው ዋናውን የዘመኑን ጉዳይ በትንትኒት የተነገረለት የመሲሁን መምጣት በምልክቶቹ መሠረት ማገናዘብና ማወቅ ስለተሣናቸው ሲሆን ይህም ተግሣፅ ለእኛ ለምሳሌ ተፅፏል።

በዓለም ዙሪያም ሆነ በሀገራችን ኢትዮጵያ የምናየውና የምንሰማው ዘመኑን እንድንዋጅ እንድናስተውልና ከክፉው በመጠበቅ ለማይቀረው መንፈሳዊ ውጊያ እንድንዘጋጅ ያበረታታናል፣ ያሳስበናል።

የእስራኤል ሕዝብ በዘመናቸው የሚከሰቱ ሁኔታዎችን የሚያገናዝቡ በመጠበቂያ ማማ ላይ ሆነው ሊመጣ ያለውን የሚጠቁሙ ሕዝቡን ከመታረድ እንዲያመልጥ የሚያስጠነቅቁ ነቢያት እንደነበሩት ዛሬም በዘመናችን ሠይጣን፣ ዓለምና ስጋችን ለዘላለም ሞት እንዳይዳርጉን የሚያስጠነቅቁን የእግዚአብሄር ሕያው ቃልና የእግዚአብሔር ትጉህ አገልጋዮች አሉልን።

ቅዱስ መፅሐፍን አናነብም ብለን ወይም የሚመክሩ የሚገስፁ ቄሶች መጋቢዎች፣ ዲያቆናትና ዘማሪዎችን መልዕክት አልሰማ ካለማለታችን በስተቀር እግዚአብሔር ዛሬም ከመናገርና ዘመኑን ከመግለፅ አይመለስም።

ስለ መጨረሻው ዘመንና ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት በማቴዎስ ወንጌል ሃያ አራተኛውም ምዕራፍ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ከሞላ ጎደል በተፈፀመውበትና በሚፈፀመውበት ዘመን ላይ ሆነን ለቅዱስ ቃሉ ጥናትና ምስክርነት ቸልተኞች ብንሆን ዘመኑን እንዳልዋጀን ዳተኞችና እንቅልፋሞች ዘይታቸው እንደጐደለባቸው ሠነፍ ደናግላን ሚዜዎች መሆናችንን አጥብቀን እንረዳ።

በሠገነቱ የላይኛው ክፍል የጌታን የተስፋ ቃል በመጠበቅ በፀሎት ይተጉ የነበሩት ደቀመዛሙርት በትክክል ዘመኑን በመዋጀታቸው ሀያሉ የእግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ መላት እንደ እሣት በተከፋፈሉ ልሳኖች ወርዶባቸው ዓለምን በመሉ እኒያ ጥቂት ሰዎች ነቀነቁት!

ዛሬስ የክርስቶስ ደቀ መዛሙት (ተከታዮች) ቁጥራችን በቢሊዮኖች እየተቆጠረ ጉልበት ያጣነው የዓለም መሣቂያ የሆነው የተልፈሰፈስነው ዘመኑን ባለመዋጀታችንና የተባረከውን የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ባለመሞላታችን ነው። «ዘመኑን ዋጁ ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጅ ሞኞች አትሁኑ» (ኤፌሶን 5÷17)

በኃጢአት በጨለማው ዓለም የክርስቶስ ፀዳሎች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ሲሆን ዓለማችን ግን በክፉ የጨለማ ኃይላት እጅ መወደቋንና ብርሃን ማጣቷን የምናያቸውና የምንሰማቸው የጨለማ ሥራዎች ይመሰክራሉ። "በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ" /ዮሐ. 9÷5/ "እነሱም ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸውም ደንደናነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ" /ኤፌሶ. 4÷18/

በዚህ የጨለማ ወቅት ታዲያ የብርሃኑ የክርስቶስ ጸዳሎችና ፍንጣቂዎች የሆኑ ደመቀዛሙርቱ ወይም አማኞቹ ምን ያህል እንደሚፈለጉ ማንም የሚረዳው ነው።

ምንም እንኳን በእምነታቸው የተነሳ መገፋትና መሰደድ ቢደርስባቸውም ክርስቶስን አምነው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሕይወታቸው የተቀየረ ሰዎችን የሥራ ኃላፊዎችና የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ለምክራና ለኃላፊነት ዘወትር እንደሚጠሯቸው እኛ ምስክር ነን።

ለእስራኤል ሕዝብ መሪነት በእግዚአብሔር የተመረጠው ሙሴ በበረሀ የተገለጠለት በቁጥቋጦ የታየው የጌታ ብርሃን ዛሬም በቅዱስ ቃሉ አማካኝነት በሰዎች ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ እሣትን እየፈጠረ ጨለማውን እያስወገደ ብዙዎችን ወደ ብርሃን አምጥቷል።

የክርስቶስ ዘላለማዊ ብርሃን በመስቀል ላይ ጣሩና ሞቱ ከጐኑ የወጣው ውሃና ደምን አልፎ ለዓለም ቅዱሣን ሁሉ የፍንጣቂ ፀዳል በመሆኑ በማያምኑት ዘንድ መቋቋም የማይችሉት ብርሃን ሆኖባቸዋል።

በልዩና ሰው ሊቀርበው በማይቻል ብርሃን ውስጥ ተከብቦ ያለው ጌታ ልጆቹንም በሄደበት እየባረከ ባለብርሃን አድርጓቸዋል።

ዓለም የክርስቶስ ብርሃን ፀዳሎች

እራሱ ጌታ ተከታዮቹ በእሣት ሊያጠምቅ እንደሚመጣ አስቀድሞም ለትንቢት ተነግሮለታል። "እርሱ በመንፈስ ቅዱስ እሣትም ያጠምቃችኋል" /ማቴ. 3÷11/

ይህ የክርስቶስ ብርሃን በጨለማው ዓለማችን ውስጥ የክርስቶስ ተከታዮች በሚገኙበት ሥፍራ ሁሉ በብሩክ ቃላቸውና ሕይወታቸው ይበራል፤ ይንፀባረቅል። ባይናገሩም እንኳን የክርስቶስ ተከተዮች የታተሙበት ወርቅማ እሣት የመንፈስ ቅዱስ ማህተም በላያቸው ላይ የሚንፀባረቅ ጭምትነት፤ ገርነት፤ የዋህነትና ፍቅርን የሚያሳናዕፍ ልሳን ነው።

የክርስቶስ ብርሃንና እሣት ፈፅሞ የማይጠፋ ሆኖም ግን አልፎ አልፎ የተዳፈነ በሰዎች ውስጥ የታመቀ መለኮታዊ ብርሃን ነው።

ዛሬም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ይህ የመንፈስ ቅዱስ እሣት የነካቸው፤ ያበራላቸው፤ የለኮሳቸውና ያቀጣጠላቸው የክርስቶስ ተከታዮች በገጠርም ይሁን በከተማ በሰሜን ይሁን በደቡብ በምሥራቅ ወይም በምዕራብ በተቀደሰ ህይወታቸውና አገልግሎታቸው በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ዙሪያ የክርስቶስ ጸዳል ሆነው የእርሱን ብርሃን ያንፀባርቃሉ። "እንደ መስታወት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን እንደሚደረግ ጌታ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" /2ኛቆሮ. 3÷18/

የሚቃጠል ልብ ያላቸው ይፈለጋሉ!

ለክርስቲያን አገልጋዮች በመንፈስ ቅዱስ ከሚቃጠል ልብ የተሻለ ሌላ ነገር ምንም አይፈለግባቸውም። ግለኝነትና እራስ ወዳድነት በሰፈነበት ዘመናችን ዓለማዊነትን ክዶ ክርስቶስን መምሰል የሚቻለው በመንፈስ እንዲቃጠሉ ለጌታ የተሰጡ አገልጋዮች ልጆቹ ብቻ ነው።

የእግዚአብሔር አንጋፋ አገልጋይ ዶክተር ቢሊ ግርሃም እንደተናገሩት ክርስቲያኖች በእርግጥ በመንፈስ ቢቃጠሉ ዓለም የሚቀጣጠል ነገር ግን ማየት ስለምትወድ ልጆቿን በመላክ መንፈሱ ክፋታቸውን ባቀጣጠለው ነበር። "በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ" /ሮሜ. 12÷11/

የእግዚአብሔር መንፈስ በልቡ የሚቃጠልበት ሰው አጀንዳው፤ ሐሳቡ፤ ንግግሩ፤ ውለው አመለካከቱና ጽሁፍ ሁሉ ክርስቶስን ይሸታሉ።

"እሳትህን ላክ እሳትህን ላክ ጌታ!" በተዘመረባቸው የኢሊባቦር የቤቴል ማህበር ምእመናን ወገኖች ላይ በትክክል የእግዚአብሔር እሳት ፈሰሰባቸው የተሰጣቸው ዝማሬና የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ስጦታዎች አያሌዎችን ወደ ወንጌል አማኞች ህብረት እንዳመጣ የሚመሰክሩ በህይወት ዛሬም አለ።

የመንፈስ ቅዱስ እሣት በመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ የተሀድሶ አማኞች ላይ የፈሰሰው ጸጋ በሚገኘው በ1880ዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባቸው የአፋ መፍቻ ቋንቋ በማጥናታቸው ነበር።

የመንፈስ ቅዱስ እሳት በክርስቶስ ደቀመዝሙረነት ላይ በፈሰሰ ጊዜ አንዱ የሌላውን ቋንቋ መስማት አልተቸገረም ነበር። /ሐዋ. 2÷11/

የመንፈስ ቅዱስ እሣት በተገፋ ጊዜ ግን ሰዎች ቋንቋቸው ይደባለቅና አንዱ ለእራሱ ወገን የሚናገረውም ሳይቀር የማይገባው ይሆናል። መለያየት መባላቱም ይሰፋል (ዘፍ 11፤7)

በቤተክርስቲያን ታሪክ በመፈንስ ቅዱስ ልባቸው የተቃጠለ አያሌ ሰዎች የተነሱ ሲሆን እነዚህ ሰዎች ለዚያ ክቡርና ቅዱስ የተቀጣጠለ ሕይወት የበቁት እየጸለዩ የሚመክሩ አጽናኝ ወገኖች በመኖራቸው ነው። "ስለዚህ ምክንያት እሳት እንደሚቀጣጠል ሰው እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሳሳ አሳስብሀለሁ" /2ጢሞቲ. 1÷6/

ስለዚህ ከሰዎች አእምሮና መረዳት በላይ በሚሰራው ቅዱስ መንፈሱ የሚያቀጣጥለን እግዚአብሔርን በየዕለቱ ከልባችን በመፈለግ ልባችን ሊቀጣጠል ይገባዋል።

የእግዚአብሔር እሳትም እንደሰደድ እሳት ያገኘውን ሁሉ የሚያቃጥል አይደለምና በቅዱስ እሣቱ በቅዱስ ሥርዓቱ ጌታ እንዲያገኘን በጥሞና እንገለጽ!!!

ከተሃድሶ በፊት በተሰበረ ልብ ንሰሃ ይቀድማል

ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ በተዘገቡ አያሌ መንፈሳዊ ተሃድሶዎች እንደተረጋገጠው መንፈሳዊ ተሃድሶውን የሚቀድመው እውነተኛ የተሰበረ ልብ ንሰሃዎች ታየተዋል።

በፍጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ይሹ ዘንድ ቃልኪዳን አደረጉ፣ የእስራኤልንም አምላክ እግዚአበሔርን የማይፈልግ ታናሽ ወይም ታላቅ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን ይገደል ዘንድ ማሉ። ለእግዚአብሔርም በታላቅ ድምፅ በእልልታ በእምቢልታና በቀንደመለከት ማሉ። በፍጹም ልባቸው ምለዋልና በፍጹምም ሀሊናቸው ፈልገውታልና እርሱም ተገኝቶላቸዋል። ይሁዳ ሁሉ በመሐላቸው ደስ አላቸው እግዚአብሔርም በዙሪያቸው ዕረፍት ሰጣቸው (2መዋእዜ 15:14)

የንሰሃ እውነተኛነት የሚለካው ከልብ በመደረጉ ሲሆን የእግዝአብሔርን ልብ ከሰው ልብ ጋር በማገናኘት ክፉውን የሰው ልብ ቅዱስና መልካም አድርጐ ለበጐ ሥራ ያዘጋጀዋል።

አካንን የመሰለ እርም ደባቂ ወይንም አናኒያንና ሰጲራን መሰል ከእግዚአብሔር ቸርነት ላይ አጉዳይ ቀጣፊ እስኪቀየሩ ድረስ ሁሉንም የሚፈውሰውና የሚያስተካክል ሁለንተናዊ ለውጥን የሚያስከትል የመንፈስ ቅዱስ የማንባት ሥራ ይካሄዳል።

እግዝአብሔር በደልና ቁርሾ ባለበት ክንዱ አይገለጥም፣ ምህረቱ የበዛው ጌታም በረከቱ በስፋት አይለቀቀም።

“ አቤቱ መርምረኝ ልቤንም እወቅ ፈትነኝ መንገዴንም እወቅ በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ የዘላለምንም መንገድ ምራኝ“ (መዝሙር 138:23)

ሶስት ሺህ ሰዎች ወደ ክርስቶስ መንግሥት ከመግባታቸው በፊት በሐዋሪያው ጴጥሮስ በተነገራቸው ቃል መሠረት መሲሁን ኢየሱስን በመካዳቸውና ለሞት አሳልፈው በመስጠታቸው ተፀፅተው እውነተኛ ንሰሃ በማካሄዳቸው ታላቁ ተሃድሶ በአይሁድ ማህበረሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ተካሄደ (ሐዋርያት 2: 37)

እውነተኛ ንሰሃ ከስሜት በላይ የሆነ ነገር ግን ስሜትንም የሚቆጣጠር የአንድን ሰው ጠቅላላ ማንነት የሚያጠቃልል አቅጣጫን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚያስቀይር ነው።

በአውሮፓ የተሃድሶ ዘመን ጌታ እግዝአብሔር ከመብረቅ አደጋ፣ ከሮማ ጳጳስ ሰይፍና ከተቀናቃኝ አመባዊ ሃይማኖተኞች የተረፈው ዶ/ር ማርቲን ሉተር ትልቁን የተሃድሶ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት በተሰበረ ልብ ትክክለኛ ንሰሃ አድርጓል። “በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ “ (ሮሜ 12: 2)

እውነተኛ መታደስን የሚለማመድ ልብ ምልክቶች

በቤተክርስቲያን ተሃድሶ ወይንም ወደ እውነተኛ ና ወደቀደመችው የጥንት የሐዋሪያት ማህበር ልምድ መመለስ እንቅስቃሴ ላይ የሚከተሉት ነጥቦች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልክቶች ናቸው።

1) አንድ ሰው ኃጢያቱ እየተሰማው እራሱን መርዳት እንደማይችል ተረድቶ ክርስቶስንና ቅዱስ መንፈሱን ለብርታትና ለፈውስ ይፈልጋል።

2) ከጌታ ጋር የሚያደርገው ህብረት ክርስቶስን በመፈለግ ብቻ ላይ ይሆናል። የቤተ ክርስቲያን አባልነትና ዓይነት የአገልግሎት ደረጃን እውቅና ምኑም አይደለም።

3) ከማንኛውም ዓይነት የኃጢያት ሰብዕና ልምምድ ዛሬውኑ ነፃ የመሆን ፍላጐት ያድርበታል። ድልን ይናፍቃል።

4) ክርስቶስን መከተሉ የሚያስከትለውን ዋጋ ተምኖ የቆረጠ ነው። መሰደድና መገፋት የሚጠብቃቸው ይሆናሉ።

5) ለእግዚአብሔር መማረክና ለቅድስናቱ መገዛት ትልቁ መሻቱ ነው።

6) በእግዚአብሔር ላይ የሚደገፉና የሚያርፍ ልብ ሲኖረው የየዕለቱ ተግባሩንም እንደጥሞና በደስታና በሐሴት ይፈጽማል።

7) የምስጢር ጸሎት በየቀኑና በየሰዓቱ የሚያካሂድ ከጌታ ጋር ግንኙነት ሲቀዘቅዝ እንደበድን የሚከብደው ይሆናል።

8) የእግዚአብሔርን ቃል በየዕለቱ ለማንበብ ጥማት ያለው ተግሣጽንም ከቃሉና ከወገኖች ለመቀበል የተዘጋጀ ልብ ይኖረዋል።

9) የእግዚአብሔር ክብር ከማንኛውመ ክብር ሁሉ በላይ ይቀድምለታል።

10) የእግዚአበሔርን ፍቅር ለዓለም ለማንፀባረቅና እያንዳንዱን ቀን ይጠቀምበታል።

11) ላለመሰናከል የሚጠነቀቅ የክርስቶስን ስም ላለማሰደብ የሚጣጣር ነው።

12) የክርስቶስ ጸጋና እውቀት ዘወትር ማደግን የሚመኝና መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ እንዲፈስስ የሚጋብዝ ይሆናል።

እነዚህ ምልክቶች በአብዛኛውን ጊዜ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ተነክተው መንፈሳዊ ተሃድሶ በሚጀምሩበት ጊዜ የሚከሰቱ ተጨባጭ ምልክቶች ናቸው።

የግል ፀሎት፣ የቃሉንባብ ጊዜና ጥሞና እጅግ ተፈላጊ የመንፈሳዊ ተሃድሶ አካላት ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ መንፈሳዊ ተሃድሶ ላይ ያለ ሰው ከግል ምቾቱ ይልቅ እራሱን በመካድ ለክርስቶስ ማደረን ይመርጣል።

እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ ጭምትነት ያለበትን ጽድቅ የሆነውን ንጹህ የሆነውን ፍቅር ያለበትን መልካም ወሬ ያለበትን በጐነት ቢሆን ምስጋና ቢሆን እነዚህን አስቡ። (ፊልጰስ 4:8)

መንፈሳዊ ተሀድሶና ቤተሰባዊ ጉዳዮች

ስለ ግል መንፈሳዊ ሕይወታችሁና ስለቤተክርስቲያ መታደስ ስታስቡ የቤተሰባችሁንም ጉዳይ ታስባላችሁን? የክርስቶስ ዳግም ምፅአት ቤተሰባችሁ ያስታወሳልን?

«ዳሩ ግን የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቧል። እንግዲህ እንደባለአእምሮ አስቡ፣ ትፀልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ» (1 ጴጥሮስ 4÷7)

ብዙዎች በጨለማው ዓለም የተያዙ ቢሆንም ቤተሰባችን ግን ከዚህ ጨለማ የወጣ እንጂ በጨለማው የያዘ ሊሆን አይገባውም።

ጊዜው ለእራሳችን በመሞት ለክርስቶስ የምንኖርበት ሲሆን እራስ ወዳድነትና የምኞትና የቅንጦት ዝንባሌዎች በመንፈስ ቅዱስ እሣት የሚራገፉበት ጊዜ ነው።

ጌታ መንፈስ ቅዱስ በመላት በቤተሰባችን ውስጥ ሊሰራ የሚፈልግበት ወቅት ላይ እንገኛ ለን። በመጨረሻው ዘመን በስጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ የሚለው ቤተሰብን በሚገባ ያጠቃልላል (ኢዩኤል 2:28)።

ከጨለማው የሰይጣን መንፈሳዊ ሰራዊት ጋር በምናደርገው የእለት ተእለት ውጊያ አንዳች ጊዜ በከንቱ መባከን የለበትም። ሆኖም ግን ቤተሰብንም ጊዜ ሰጥቶ ያለማስተናገድም እርም ስለሆነ ሁሉንም በሚዛናዊነት መምራት ያሻል። «ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር»(ጢሞ 3:4)።

መንፈሳዊ ተሀድሶ በቤተሰባችን ዘንድ እንዲሰፍን ለቤተሰባችን በመፀለይ የጌታን ክንድ መገለጥ እንጠይቅ፣ ሌሎች ቤተሰቦችንም ለክርስቶስ መውረስ እንድንችል ጌታን እንማፀነው። ከቤተሰባችን አባላት ጋር አገልግሎታችንና ፀሎታችንን እንጋራ፣ እንካፈል።

የቤተሰባችንን ምስጢራዊ ጉዳዮች የልጆቻችንንም ሳይቀር በሚገባ እንጠብቅላቸው። ለፀሎት፣ ለምስክርነትና ለዝማሬ ወላጆች ተምሳሌቶች እንሁን። ታላላቆችም ለታናናሾች።

ያላመኑ የቤተሰብ አባላትን በፍፁም ፍቅር እንሸከማቸው። ጌታ አንድ ቀን ምርኮ ይሰጠናል በሚል ተስፋ ሳንታክት እንከባከባቸው፣ እንፀልይላቸው።

የአንዱ የቤተሰቡ አባል መዳን ለሌላው በረከት ነውና የእግዚአብሔር ሙሉ ጉብኝት እስኪመጣ ድረስ ፀሎታችንና የሕይወት ምስክርነታችን በፍቅር ይስፋፋ።

«በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ» (ሐዋርያት 16:31)

እግዚአብሔር አምላካችንን አባታችን ብለን ልንጠራ ትልቅ መብት ያገኘን ክርስቲያኖች ሁላችን አንድ የክርስቶስ ቤተሰብ መሆናችንን እያሰብን ይህን የክርስቶስ ቤተሰባዊነት መጀመሪያ በራሣችን ቤት እንለማመደው። (ኢያሱ 24:15)።

«እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን»

ዓለም ዓቀፍ የፀሎት ርዕሶችና ዘገባዎች

«ታላቁ ጴንጠ ቆስጤ/በአለ ሃምሳ ዕለት» የሰኘ መጠሪያ ያለው ዓለም ዓቀፍ የፀሎት ቀን ጁን 4 ወይም ግንቦት 28 ዕሁድ ቀን ስለተጠራ በያላችሁበት ህብረት በዚህ የዓለም ዓቀፍ ፀሎት ቀን እንድትሣተፉ እንጠይቃለን።

በሞዛምቢክ ብዙዎች አመኑ

በደቡባዊ አፍሪካዊት ሀገር ሞዛምቢክ አያሌ ስዎች የኢየሱስ ክርስቶስን እምነት ተቀብለው ከማህበር ምእመናን ጋር ተቀላቅለዋል። ጌታን ስለዚህ ድንቅ የማዳን ስራው እያመሰገንን አማኞቹም ፀንተው እንዲገኙ እንማለድላቸው።

በኢትዮጵያና በሌሎች ሀገሮች ስለሚደጋገመው ርሀብና የፖለቲካ ቀውስ እንፀልይ

በሰሜን ኬንያና በኢትዮጵያ አንዳንድ ክፍሎች የተከሰተው ድርቅን ጌታ እንዲታደግ፤ በኢትዮጵያም ከግንቦቱ 1997 ምርጫ በኋላ የተከሰተው አላስፈላጊ የደም መፋሰስ ጦስና ጥላቻን ክርስቶስ በደሙ እንዲፈወስ እንፀልይ።

በአጠቃላይ ለመንግሥታትና ለፖለቲካ መሪዎች እግዚአብሄር የማስተዋል ጥበብን እንዲሰጣቸው እንማለድላቸው።

እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይሻለኛል?

1. በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተም ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ (ሐዋርያት 16:31)።
2. ሕይወታችን እንዲስተካከልና እንዲታደስ ኃጢአታችንን በመናዘዝ ንስኃ እንግባ (ሮሜ 3:23 6:23 ኢሳይያስ 55፣7)
3. ለኃጢአታችን የተሰቀለውንና የሞተውን በሦስተኛውም ቀን ከሙታን የተነሳውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከቅዱስ ቃሉ በመስማት እንታዘዘው (ማርቆስ 10:33 ዮሐንስ 1:12)

ማሳሰቢያ

አንባቢዎቻችን ስለምትልኩልን የሀሳብ የፀሎትና የገንዘብ ድጋፍ ከልብ እናመሰግናለን። ለሁላችሁም ለመመለስ አቅመ ስለሌለን በዚህ አጋጣሚ ሠላምታችንን እናቀርባለን። ለአገልግሎቱ መቀጠል አሁንም ትብብራችሁን በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን።

የምፅአቱ የምሥራች የወንጌል መነቃቃት
የትርጉም አገልግሎት

ትርጉም ቅንብርና አስተባባሪ፣
አደፍርስ ሀብቴ መካሻ
አሳታሚ፣ ሪክ ካርማይክል
የስልክ ቁጥር 190612
የፖ.ሣ.ቁ 8986
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ